# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## የ1998 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

**(Editing and Coding Manual)**

ሚያዚያ 1998
አዲስ አበባ

# የ1998 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት የመጠይቅ ዕርማትና ኮድ አሰጣጥ መመሪያ

# (Editing and Coding Manual)

## I. መግቢያ

የሰው ኃይል ስታትስቲክስ መረጃዎች ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ዕቅዶችን ለመንደፍ ስለአፈፃፀማቸው ለመከታተልና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመውሰድ መሠረታዊ በመሆናቸው በየወቅቱመረጃዎች በመስኩ እንዲሰበሰቡ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሠረት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በሚያዚያ ወር 1998 ዓ.ም የከተማ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ሁኔታ ጥናት በማድረግ መረጃ ሰብስቧል፡፡ ጥናቱ ግቡን እንዲመታ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ስራዎች መካከል አንደኛው ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚገባ አርሞና ኮድሰጥቶ ለሚቀጥለው የሥራ ክፍል/ ዳታ ኢንትሪ/ ማስተላለፍ ነው፡፡

ስለሆነም የኮድ አሰጣጥና ዕርማት የማድረግ ተግባር በጥንቃቄ መከናወን ይኖርበታል፡፡ በተለይም በዚህ ጥናት ከተካተቱት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎች፣ እነዚህንም ጥያቄዎች እርስ በርስ ለማመሳከር ከሚፈጥረው ውስብስብ አሠራር አኳያ አራሚው የጥናቱ የመረጃ አሰባሰብ በቂ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ በተጨማሪ የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም የአገልግሎት መረጃ ኮድ ሲደረግ በመጠይቁ የተሞሉትን መረጃዎች በጥሞናና በእርጋታ ማየትና መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም በመጠይቁ እርማትና ኮድ መስጠት ሥራ የሚሳተፉ ሠራተኞች የጥናቱን ውጤት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ የሥራ ድረሻ የተጣለባቸው መሆኑን አውቀው የእርማትና ኮድ አሰጣጡን መመሪያ በደንብ መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## II. አጠቃላይ መመሪያ

### ሀ. ኤዲቲንግ:

ከልዩ ልዩ ጥናቶች የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ኤዲት ማድረግ /ማረም/ የመረጃውን ጥራት ለመገምገምና እንደዚሁም ስህተቶችን፣ የሚቃረኑ መረጃዎችን፣ ሳይሞሉ የቀሩትን፣ ...ወዘተ በማረም የመረጃውን ጥራት ለማሻሻል ይረዳል፡፡

ኤዲቲንግ ማለት የተሰበሰበውን መረጃ ሁኔታ በመመልከት በተሰጠው መመሪያ መሠረት አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ ይህንን ሥራ በሚያከናውንበት ወቅት

የመረጃ መሰብሰቢያው ፎርም /መጠይቅ/ ለመረጃ ሰብሳቢው በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ኤዲተሩ /አራሚው/ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 1. ሳይሞሉ የቀሩ መረጃዎች

በመጠይቁ ሳይሞሉ የቀሩትን መረጃዎች በመፈለግ መመሪያውን በመከተል አስፈላጊውን እርማት ማድረግ ነው፡፡ ሣይሞሉ በቀሩ መረጃዎች ፋንታ የሚሞላው መረጃ የሚገኘው ሌሎች የተሞሉ መረጃዎችን በማገናዘብና በመመርመር ነው፡፡ በተቻለ መጠን ለተዘለሉና ሣይሞሉ ለቀሩ መረጃዎች በሙሉ አስፈላጊው እርማት ተደርጐ መሙላት የሚያስፈልግ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ሣይሞሉ ለቀሩት መረጃዎች በፎርሙ /መጠይቁ/ ከታዩት መረጃዎች አኳያ አመሳክሮና መርምሮ ለማረም የማይቻል ከሆነ በፈጠራ መሙላት ስለማይገባ ሣያርሙ ዓምዱን ባዶውን መተው ይመረጣል፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ኮድ ሲደረግ ላልታወቀ መልስ የሚሰጠው ኮድ ይሰጠዋል ማለት ነው፡፡

## 2. ሊሆኑ የማይችሉና የማይመስሉ መልሶች

ሊሆኑ የማይችሉ መልሶችና የማይመስሉ መልሶችን በእርማት ጊዜ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ሊሆኑ የማይችሉ መልሶች በመመሪያው ከተሰጠው ውጭ የተመለሱ መልሶች ሲሆኑ ለምሳሌ፣ ባለፈው ሳምንት ለስንት ቀናት ሠሩ? የሚል ጥያቄ ቢኖርና በዓምዱ የሰፈረው ቀናት ብዛት ከ7 ቀን በላይ ከሆነ ይህ ሊሆን የማይችል መልስ በመሆኑ መታረም አለበት፡፡ የማይመስሉ መልሶችን በተመለከተ የጋብቻ ሁኔታን እንደ ምሣሌ ብንወስድ የአንድ ሰው የጋብቻ ሁኔታ፣

1/ ፈጽሞ ያላገባ/ያላገባች

2/ ያገባ/ያገባች

3/ ባል/ሚስት የሞተባት/የሞተችበት

4/ የተፋታ/የተፋታች

5/ የተለያዩ

ሲሆን ይህም መረጃ የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ለቤተሰብ አባላት በሙሉ ነው፡፡ ለአንድ ዕድሜው 11 ዓመት ለሆነ ልጅ የጋብቻ ሁኔታ "ሚስት የሞተችበት" ተብሎ ቢሞላ በዚህ ዕድሜው አግብቶ ሚስቱ ልትሞትበት ስለማይችል መልስ ሊሆን የማይችል በመሆኑ መታረም አለበት፡፡ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መልሶች ተመዝግበው ሲገኙ ከቀሩት ዓምዶች ጋር በማገናዘብ መረጃው ይታረማል፡፡

3. የሚቃረኑ መልሶች በተለያየ ዓምድ ላይ የተሞሉ መረጃዎች ለምሳሌ በዓምድ 206 እና 207 ላይ ስለትምህርት የተሞላው መረጃ መልስ ሰጪው በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት 10ኛ ክፍልን እንዲሁም በቀድሞ 12ኛን እንኳ ያልጨረሰ ቢሆንና በዓምድ 209 ላይ የስልጠናው ዓይነት ኘሮፌሽናል ቢሆን የሚቃረኑ ስለሆኑ ማረም ተገቢ ነው፡፡ የሚቃረኑ መልሶች የሚባሉት ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ መልሶች ሳይዛመዱ ሲቀሩ ነው፡፡

## 4 ጽሁፉን ለማንበብ የሚያስቸግሩ መልሶች

በትክክልና በደንብ የማይነበቡ መልሶችን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እርማቱ በሚደረግበት ወቅት የሚፃፉ ጽሁፎች ሁሉ በደንብና በቀላሉ የሚነበቡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 5. ከመመሪያ ውጭ ስለተሞሉ መልሶች /የይለፍ ትዕዛዞች ካልተከበሩ/

ለምሳሌ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነበርን ? ተብለው ለተጠየቁት መልስ "የለም" ብለው ኮድ "2" ለተሞላላቸው በሚቀጥለው ዓምድ የሥራ ሰዓት ተሞልቶ ከተገኘ የነዚህ ዓምዶች መልስ የሚቃረኑ መልሶች ናቸው፡፡ ይህም ማለት በሳምንት ውስጥ ምንም ሥራ ያልሰራን ሰው ስንት የሥራ ሰዓቶች ሠራህ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመጀመሪያው ዓምድ ላይ የተሞላው ኮድ "2" የለም የሚለውን ስህተት ሊሆን ስለሚችል ተከታታይ ዓምዶችን መርምሮ ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በዚህ ጥናት ከመመሪያ ውጭ የተሞሉ መረጃዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ የሚጠየቀው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ዕድሜው 9 ዓመት ለሆነው ህፃን የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ ተሞልቶለት ቢገኝ ምንም እንኳ ዕድሜያቸው 9 ዓመትና በታች የሆኑ ህፃናት መመሪያው ዕድሜያቸው 10 ዓመት እስካልሞላ ድረስ ስለስልጠና ጋብቻ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎች እንደማይጠበቅባቸው ስለሚገልጽ የተሞላው መረጃ ከመመሪያ ውጭ ስለሆነ መሠረዝ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የዓምዶችን ቅደም ተከተል ለማመልከት መረጃዎች ሲሞሉ ከየትኛው ዓምድ ወደ የትኛው ማለፍ እንደሚገባ በመጠይቁ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ስለሆነም መረጃዎች ይህንኑ ተከትለው መሞላት ስለሚገባቸው በመጠይቁ ላይ በተመለከተው መሠረት ያልተሞሉ መረጃዎች ከተገኙ መታረም ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በዓምድ 205 እድሜው ከ 10 ዓመት በታች እና ከ 5 ዓመት ባለይ የተሞላለት ሰው ከዓምድ 208 እስከ ዓምድ 507 ያሉት ጥያቄዎች በሠረዝ መታለፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዓምዶች ተሞልተው ከተገኙ ሌሎች ዓምዶችን በማገናዘብ ማስተካከልና ማረም ያስፈልጋል፡፡

## 6. በጽሑፍ የተሰጠ መልስና ኮድ አለመጣጣም

በመጠይቁና በመመሪያው ውስጥ በግልጽ እንደተመለከተው ለአሠራር ያመች ዘንድ መረጃዎች በኮድ ብቻ (ከጥቂት ዓምዶች በስተቀር) እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡ሆኖም አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች በስህተት መልሶቹን በቃላትና በኮድ ሊመዘግቡ ይችላሉ፡፡ ይህ አሠራር በተለይ መረጃዎች በኮምፒውተር በሚቀነባበሩበት ወቅት ችግር ስለሚፈጥሩ በቃላት የተመዘገቡትን መረጃዎች ከሚጣጣመው ኮድ ጋር ተገናዝቦ መሞላት ይገባዋል፡፡ስለዚህ በጽሑፍና በኮድ የተሰጠው መልስ ሲለያይ ሌሎች ተዛማጅ ዓምዶችን መመልከት ተገቢውን እርማት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የ1998 ዓ.ም. የከተማ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ወቅት ጥናት የኤዲቲንግ ኮዲንግ ክፍል አስተያየት መከታተያ ቅጽ በዝርዝር የተገለጠ መሆኑ ይታወቅ፡፡

## ለ. ኮዲንግ፡-

ኮዲንግ ማለት በፎርሙ የተሰጡትን መልሶች ወደ አሀዝ መለወጥ ነው፡፡ ይህም አሀዝ በቀላሉ መረጃውን በኮምፒውተር ለማቀነባበር ይረዳል፡፡ የእርማትና (Editing) የኮድ የማድረግ ተግባር በማጣመር ይካሄዳል፡፡ በዚህ ፎርም የተሞሉት መረጃዎች በአብዛኛው አስቀድመው ኮድ ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ ጾታ፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ...ወዘተ ናቸው፡፡ ለነዚህ መልሶች የእርማት ተግባር ለማከናወን ኮዶቹ በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

እንደ አዲስ ኮድ መደረግ ያለባቸው መልሶች ደግሞ በክፍል 1 የተገለፁት የአካባቢ መለያ መልሶች ናቸው፡፡ እነዚህን መልሶች ኮድ ለማድረግ የሚረዱ የኮድ ዝርዝር ይሰጣል፡፡ ይህ የኤዲቲንግ ኮዲንግ መመሪያም የአሠራሩን ሁኔታና ዘዴ የሚገልጽ ጽሁፍ ነው፡፡

- የእርማቱና ኮድ አሰጣጡ ሥራ መከናወን ያለበት ለዚሁ በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት መሆን እንዳለበት ማስታወስ ይገባል፡፡ አንዳንድ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሱ ነገሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄዎቹን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማቅረብ መፍትሔ እንዲሰጠው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ሥራውን ለማከናወን መነሻው በመስክ የተሞላው መረጃ ስለሆነ አስቀድሞ እያንዳንዱ መጠይቅ መሞላቱንና ተሟልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ቆጠራ ቦታ ለ30 ቤተሰቦች መረጃ ተሞልቶአል፡፡ ለእያንዳንዱ ቤተሰብም አንድ ባለ 3 ገጽ /A3 Size/ መጠይቅ የተሞላ ሲሆን፣ ተጨማሪ መጠይቅም ተሞልቶላቸው ከሆነ ሁለት ባለ 3 ገጽ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አንዳንድ በመረጃው አሰባሰብ ጊዜ ያጋጠሙትን ሁኔታዎች የሚያብራሩና ከመጠይቁ ጋር ተያይዘው የመጡ አስተያየቶችን በሚገባ መያያዛቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

- እርማት በሚደረግበትና ኮድ በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ሥራው ከሚመለከተው ኃላፊ ካልታዘዘ በስተቀር ማንኛውም በመረጃ ሰብሳቢው የሰፈረው ነገር መፋቅ/መጥፋት የለበትም፡፡ መረጃውን እርማት የሚያደርግበት ከሆነ ካሰፈረው መረጃ አጠገብ መረጃው ከተፃፈበት ቀለም በተለየ ቀለም እርማቱ ይደረጋል፡፡

# III መጠይቆችን ማረም

## ክፍል 1፡- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ከዓምድ101 እስከ ዓምድ 108 ያለውን የክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ወረዳ/ክ/ከተማ ቀበሌ ስሞች በመጠይቁ ሽፋን ገጽ ላይ እና በየመጠይቆቹ አናት ላይ ተሞልተዋል:: እነኚህ ከክልል እስከ ቀበሌ ላሉት ዓምዶች ካርድ ኮለሞቹ መስክ ላይ የተሞሉ ስለሆነ፣ በተለይ ተዘጋጅቶ የቀረበውን የአካባቢ መለያ ኮድ መጽሐፍ በመጠቀም ካርድ ኮለሞቹ በትክክል ተሞልተው መምጣታቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: የቆጠራ ቦታ ኮድ በትክክል መሠጠቱን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: እንዲሁም ጥናቱ የተካሄደበት የቅ/ጽ/ቤት ስምና ኮድ ካርድ ኮለም መሞላት አለባቸው::

ዓምድ 101-103 ፡- **ክልል፣ዞን፣ወረዳ**፡- ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል፣ዞንና ወረዳ ስም ና ኮድ በዓምዱ በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ አለበት::

ዓምድ 104 : -**ከተማ**፡ -ከከተማው ጥናት የተመረጠው የከተማ ስም በተሰጠው ቦታ በትክክል መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ኮዱ ደግሞ በካርድ ኮለሞች ይሞላል:: በካርድ ኮለሞቹ /Area Code Book/ ተስማሚው ኮድ መስጠቱ ይረጋገጣል::

ዓምድ 105: -**ከፍተኛ/ ወረዳ/**: - ጥናቱ በከተማ የተካሄደ ስለሆነ የከፍተኛው/የወረዳ የክ/ከተማው ስም ፣በዓምዱ በተሰጠው ባዶ ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 106: - **ቀበሌ**: - በከተማው ውስጥ ቀበሌው የሚጠራበት ስም/ቁጥር በተሰጠው ቦታ መሞላቱን ማረጋገጥ እና በካርድ ኮለሞቹ ደግሞ የቀበሌው ኮድ ከአካባቢው መለያ ኮድ በመጠቀም በካርድ ኮለሞቹ /Area Code Book/ ተስማሚው ኮድ መሰስጠቱ ይረጋገጣል::::

ዓምድ 107: -**የቆጠራ ቦታ**:-የቆጠራ ቦታ ኮድ በካርድ ኮለሞቹ በትክክል መሞላቱን ማጤን ያስፈልጋል:: ለከተማ የቆ.ቦታ በሦስት ዲጂት /Digit/ መሞላቱን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 108: - **የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር**:- በአንድ የቆጠራ ቦታ በጥናቱ የሚመረጡ ቤተሰቦች በጠቅላላ ብዛት 30 ነው:: ስለሆነም በዚህ ዓምድ ባሉት በካርድ ኮለም የተሞሉት ቁጥሮች ከ01 -30 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ109:- **የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም** : - በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም መፃፉን እንዲሁም በክፍል 2 ዓምድ 202 በመጀመሪያ ተራ ቁጥር ላይ መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ባይሆን ግን ከተቆጣጣሪው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ማስተካከል ያስፈልጋል::

ዓምድ 110:- **ቅ/ጽ/ቤት**

በዚህ ዓምድ የቅ/ጽ/ቤቱ ሥም በዓምዱ በተሰጠው ቦታ ተሞልቶ ለቅ/ጽ/ቤቱ የተሰጠው መለያ ኮድ ደግሞ ከዓምዱ ሥር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ዓምድ 111:-**የቆጠራ ቦታ ተከታታይ ተራ ቁጥር**

ከተዘጋጀው ኮድ መጽሐፍ /Code Book/ ለዚህ ቆጠራ ቦታ የተዘጋጀው ኮድ በሦስቱ ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ዓምድ 112:- **የቀጠለ መጠይቅ አለ?**

ከተሞላው መጠይቅ በተጨማሪ የቀጠለ ወይም የተጨመረ መጠይቅ መኖሩንና አለመኖሩን የሚረጋገጥበት ስለሆነ መጠይቁ ታርሞ ከማለቁ በፊት በጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል:: የተሞላውን ኮድ ምልክት መሠረት በማድረግ የቀጠለ መጠይቅ አለመኖሩን ማጣራትና ተገቢውን እርማት ማድረግ ተገቢ ነው:: የቀጠለ መጠይቅ ካለ ከዋናው መጠይቅ ጋር እንደአመቺነቱ በስቴፕ ለር መያያዝ ይኖርበታል::

# ክፍል 2፡ ስለቤተሰብ አባላት ዝርዝር መረጃ

## ከዓምድ 201-205 ለሁሉም የቤተሰብ አባላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ዓምድ 201፡-** ተራ ቁጥር፡-

ይህ ከ01 በመጀመር በተከታታይ ቁጥር የተሰጠበት ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡

ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መኖሩ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ « 01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 202፡-** የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም፡-

የቤተሰቡ አባላት ስም የሰፈረበት ዓምድ ስለሆነ ምንም ዓይነት እርማት አይደረግበትም፡፡

**ዓምድ 203፡-** ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና፡- በዚህ ዓምድ ሥር ባለው ንዑስ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው መሙላት ያለበት የኮድ ቁጥሮች ከ0-8 ያሉ ብቻ ናቸው፡፡ አባላቱ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚገልጽበት ኮዶች እና የተሰጠው መግለጫና ኮድ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ እና የማይዛመድ ከሆነ ኮዱን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ የኮዶቹ ዝርዝርና መግለጫቸው ከጥያቄው ሥር ይገኛል፡፡

**ዓምድ 204፡-** ጾታ፡- በዚህ ዓምድ ባለው ክፍት ቦታ መታየት ያለባቸው 1 ወይም 2 ብቻ ናቸው፡፡ ስለ ኮዱ ትክክለኛነት በዓምዱ ሥር በተሰጠው ቦታ የሰፈረውን የጾታ መለያ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም መረጃ ሰብሳቢው በስህተት ኮድ ሳይሰጥ ቢቀር ተቆጣጣሪውን በማማከር የግለሰቡን ጾታ ከልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ኮድ 9 አይፈቀድም ፆታ ካልተፃፈ ስም ታይቶ ይሞላል፡፡

**ዓምድ 205፡-** ዕድሜ፡- ይህ ዓምድ መስክ ላይ ተሞልቶ የሚመጣ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ ዓምድ ባሉት ንዑስ ዓምዶች ከ97 በላይ ቁጥር መታየት የለበትም ከ97 በላይ የሆነ ቁጥር ከታየ 97 ተብሎ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ ኮድ 99 አይፈቀድም ዕድሜ ካልተፃፈ ዝምድናና የልጆች ዕድሜ፣ የባል ዕድሜ ታይቶ በግምት ይሞላል፡፡ በተጨማሪም የዕድሜ መረጃ ካለተሞላ የቤተሰብ አመዘጋገብ ቅደምተከተልና በዕድሜ ከተገደቡ ዓምዶች ለግለሰቡ የተሞሉ መረጃዎችን በማመሳከር መረጃውን ለመሙላት ይሞክር፡፡ ይኸውም ሲሆን ከተቆጣጣሪው ጋር በመማከር የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## ዓምድ 206-207- የትምህርት ሁኔታ (ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

እነኚህ ዓምዶች የሚሞሉት ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ ስለሆነ ከ5 ዓመት በታች ለሆነ

ልጅ መረጃ ተሞልቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ በማሳወቅ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል:: በአንፃሩም ከ5 ዓመት በላይ የሆነ ግለሰብ መረጃ ሳይሞላለት ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ተገቢውን ኮድ መሙላት ተገቢ ነው::

## ዓምድ 206፡- ማንበብና መጻፍ ይችላሉ ?

ይህ ዓምድ 5 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መጻፍ መቻላቸው ተጠይቆ «አዎን» ለመለሱ ኮድ 1 «የለም» ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላበት ነው:: ስለዚህ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የሚመጡት ቁጥሮች ከ1 ወይም ከ2 ውጭ መሆን የለባቸውም:: ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በሚቀጥለው ዓምድ (ዓምድ 207) ላይ ከተሞላው መረጃ በመነሳት ማስተካከል ስለሚቻል ኤዲተሩ ለተቆጣጣሪው ማማከር አለበት::

## ዓምድ 207፡- የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?

በመጀመሪያ በዚህ ዓምድ መረጃ የሚሞላው በዓምድ 206 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ማለትም ማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ በዓምድ 206 ኮድ 2 ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ምንም ዓይነት መረጃ እንዳልተሞላ ማረጋገጥ ተሞልቶም ከመጣ ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር መረጃውን መሰረዝ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ቀጥሎም ከላይ ባለው ሰፋ ባለ ክፍት ቦታ የተጻፈው መረጃ ከሥር በካርድ ኮለሙ ውስጥ ከተፃፈው ኮድ ጋር መጣጣማቸውን ማገናዘብ ተገቢ ነው:: ለዚህም በሽፋን ገጹ ላይ ያሉትን ኮዶች መመልከት ያስፈልጋል::

| ለአምድ 207 የሚያገለግል | |
|---|---|
| የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል | |
| ኮድ | የክፍል ደረጃ |
| 01. | አንደኛ ክፍል |
| 02. | ሁለተኛ ክፍል |
| 03. | ሶስተኛ ክፍል |
| 04. | አራተኛ ክፍል |
| 05. | አምስተኛ ክፍል |
| 06. | ስድተኛ ክፍል |
| 07. | ሰባተኛ ክፍል |
| 08. | ስምተኛ ክፍል |
| 09. | ዘጠነኛ በቀድሞ |
| 10. | አሥረኛ በቀድሞ |
| 11. | አስራ አንደኛ በቀድሞ |
| 12. | አስራ ሁለተኛ ቀድሞ |
| 13. | ዘጠነኛ በአዲሱ |
| 14. | አስረኛ በአዲሱ |
| 15. | አስራ አንደኛ /preparatory |
| 16. | አስራ ሁለተኛ/ preparatory |
| 17. | 10+1/በአዲሱ የሙያ /የጨረሱ |
| 18. | 10+2/በአዲሱ የሙያ /የጨረሱ |
| 19. | 10+2 ያልጨረሱ |
| 20. | ሰርተፊኬት |
| 21. | 10+3 ያልጨረሱ |
| 22. | ዲግሪ ያልጨረሱ |
| 23. | 10+3 የጨረሱ |
| 24. | ዲግሪ የጨረሱ |
| 25. | ከዲግሪ በላይ |
| 95. | መሠረተ ትምህርት |
| 96. | መደበኛ ያልሆኑ |

## ዓምድ 208-209:- የሥልጠና ሁኔታ (ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)

ከዚህ ዓምድ በኋላ ያሉት ተከታታይ ዓምዶች የሚመለከታቸው ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ግለሰቦች ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል መረጃ ተሞልቶ አለመምጣቱንና በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪ ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ያሻል፡፡

## ዓምድ 208:- የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስደውና አጠናቀው የምስክር ወረቀት ወይም ከዛ በላይ አግኝተዋል?

በዚህ ዓምድ በሚገኘው ካርድ ኮለም አዎን ለመለሱ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዓምድ የለም መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው የሚቀጥለዉ ዓምድ ማለትም ዓምድ 209 ሳይሞላ በሰረዝ ታልፈው ወደ ዓምድ 210 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በዓምድ 207 ላይ ሠርተፊኬት፣ዲኘሎማ የጨረሱ፣ዲግሪ እንዲሁም ዲግሪና ከዚያ በላይ ተሞልቶ ከሆነ በዚህም ዓምድ የግድ ተሞልቶ መምጣት ስለሚኖርበት በዚህ ሁኔታ መሞላቱን ማየት

ያሻል፡፡ ይህ ዓምድ ሳይሞላ ከመጣ በዓምድ 207 ላይ ከተሞላው መረጃ ጋር በማገናዘብ መሙላት ይቻላል፡፡ ይህም ሲደረግ ተቆጣጣሪው ማየት አለበት፡፡

## ዓምድ 209፡- የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ዓይነት ምንድ ነው?

በዓምድ 208 የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል/ቴክኒካል) ሥልጠና ወስጄና አጠናቅቄ የምስክር ወረቀት ወይ ምከዛ በላይ አግኝቼአለሁ ብለው መልሰው ኮድ 1 የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት የሙያ (ቮኬሽናል /ቴክኒካል) ዓይነትና ተገቢው ኮድ በካርድ ኮለሙ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የሙያ ዓይነቶቹንና ተ ገቢውን ኮድ ለማገናዘብ ከታች የቀረበውን ዝርዝር ይመልከቱ፡፡

**(ሀ) ፕሮፌሽናልና፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል፣**

01 ግብርና ሳይንስ
እርሻ ኢኮኖሚክስ፣እርሻ ምህንድስና፣እርሻ
ኤክስቴንሽን ፣ የእንሰሳት ሳይን የስኬል ጥበቃ፣
አጠቃላይ እርሻ፣የደረቅ አካባቢ እፅዋትየእንሰሳት፣
ግጦሽ ሳይንስ፣ ፖስት ሃርቨስት ቴክኖሎጂ፣
የእንሰሳት ፕሮዳክሽን
02 ውሀና አፈር ጥበቃ፣
03 ደን ሳይንስ፣
04 አጠቃላይ ሕክምና
አፕቶሞሎጂ፣ፓቶሎጂ፣ኢንተርሽናል ሜድስን፣
ጋይናኮሎጂ፣ሰርጀሪ ፣ኢንስቲቲዮሎጂ፣

05 **ሜዲካል ላብራቶሪ/ራዲዩሎጂ/**

06 ፋርማሲ/ፋርማሲ ቴክኒሽያን/
07 ሳኒተር ሳይንስ
08 ክሊኒካል ሳይንስ/ነርሲንግ
09 ፓብሊክ ሄልዝ ነርስ ጤና መኮንን፣የአካባበ ጤና ፣
ፓስት ሄልዝ ኦፊሰር
10 ፐርሶኔልና ቢዝነስ ማኔጅመንት
11 ኢኮኖሚክስ
12 **ሂሣብ አያያዝ /ACCOUNTING/**
13 ሴክሬቴሪያል ሳይንስ
14 ባንክና ፋይናንስ
15 ሕግ
16 ስነጽሑፍና ቋንቋ የኢትዮጵያ የውጭ ቋንቋዎች
ስነፅሑፍ/
17 ሥነኪነት
18 ኢዱኬሽን ፔዳጐጂ
መምህርነት፣ካሪኩለም ኢንስትራክሽን፣
ኢዱኬሽን አድሚኒስትሬሽን ፣
የጐልማሶች ትምህርት
19 ጂኦግራፊ
20 ታሪክ
21 ፖለቲካል ሳይንስ
22 ሶሲዮሎጂዎና አንትፖሎጂ
23 ስነልቦና /ሳይኮሎጂ/
24 ሲቪል መሃንዲስ/ህንፃ መሃንዲስ/
25 መካኒካል መሃንዲስ
26 ኤሌክትሪካል መሃንዲስ
27 ኢንዱስትሪያል ምህንድስና
28 የማዘጋጃ ቤት ምህንድስና/አርክቴክቸር
29 ሌሎች ምህንድስናዎች
ድራይላንድ ባዩዲይቨርስቲ፣
ሃይድሮሊክስ፣ የመስኖ ምህንድስና
30 አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ
31 ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ
32 ድራፍቲንግ ቴክኖሎጂ
33 ማኒፋክቸሪንግ ቴክኖሎጂ
34 የብረታ ብረት ቴክኖሎጂ
35 የእንሰሳት ጤና አጠባበቅ (የከብት ሕክምና)
36 ኮሙኒኬሽን
37 ፓወርና የመሳሰሉት
ኢንስትሩመንቴሽን ፣
ኤሌክትሪካል ፓወር፣ ሜካኒካል ፓወር፣
ማኒፋክቸሪንግ ፓወር፣
38 ባዮሎጂ (ስነ ሕይወት)
39 ኬሚስትሪ
40 ጂኦሎጂ
41 ፊዚክስ
42 ማቲማቲክስ
43 ስታቲስቲክስ
44 ዲሞግራፊ

45 የኮምፒውተር ሳይንስ/ኢንፎርሜሽን
ሳይንስ
46 ጤናና የአካል ማሰልጠኛ ትምህርት
47 ሌላ ፕሮፌሽናልና መለስተኛ
ፕሮፌሽናል /ይገለጽ/

**(ለ) የሙያና ቴክኒክ፣**

48 የባልትና ሳይንስ
49 የቆዳ ሥራዎች ሥልጠና
50 የውበት ሥራዎች ሥልጠና
51 የቪድዮ ፎቶግራፍ ቀረጻ ሥልጠና
52 ሸክላ ስራ
53 ሽመና
54 እንጨት ሥራ /የአናጢነት ስልጠናን
ይጨምራል/
55 ኤሌክትሪክ ሥራ
56 ብረታ ብረት ብየዳና ቅጥቀጣ
57 መካኒክ /የመኪና/ የሞተር ሳይክል/
የአውሮፐላን ጥገናን ይጨምራል/
58 ግንበኝነት
59 ታይፕ
60 ልብስ ስፌት
61 ሹፌርነት
62 የልማት ተጠሪ /DA/
63 ልምድ አዋላጅ
64 ኮምፒውተር አጠቃቀም
65 በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ
/ከአጋርፋ፣ አርዳይታ፣ ባኮ፣
66 ሆቴልና ቱሪዝም
67 ፖሊስ
68 ውትድርና
69 ሌላ የሙያና ቴክኒክ /ይገለጽ/

**ዓምድ 210፡-** **የጋብቻ ሁኔታ ?**

ይህ ዓምድ እንደ «ሥልጠና ሁኔታ» የሚሞላው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ብቻ ስለሆነ ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ ግለሰቦች ሳይሞላ መምጣቱን፣ በስህተት ተሞልቶም ከመጣ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አሳይቶ መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩም ከ10 ዓመት በላይ ለሆነው ግለሰብ መረጃ ተሞልቶ መምጣት ሲገባው ሳይሞላ ከመጣ ለተቆጣጣሪው ማሳየትና ተገቢው ኮድ እንዲሞላ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1-5 ከተዘረዘሩት ውጭ እንዳልሆነ ማየት ያስፈልጋል፡፡

# <u>ክፍል 3፡-</u> ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ

<u>(ከዓምድ 301-320 ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ብቻ)</u>

<u>ዓምድ 202፡-</u> <u>መሉ ስም፡</u>- ይህ ዓምድ ከገጽ 1 ዓምድ 202 በቀጥታ የሚወራረስ ነው፡፡ ስለሆም በዚህ ዓምድ የተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር በገጽ 1 ዓምድ 202 ከተዘረዘሩት ጋር አንድ ዓይነት መሆናቸውን ማመሳከር ያስፈልጋል፡፡ በተለይም የስሞች አመዘጋገብ በሁሉም ገጾች በተመሳሳይ ቅ ደም ተከተል መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይኸም የሚያስፈልገው መረጃ አግድም Key ስለሚደረግ የአንዱ መረጃ ለሌላው እንዳይፃፍ ነው፡፡

<u>ዓምድ 201፡</u>- <u>የመስመር ቁጥር፡</u>- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ አይነካም፡፡

ሆኖም የቤተሰቡ አባላት ከ11 በላይ በመሆናቸው በተጨማሪነት ጥቅም ላይ የዋለ መጠይቅ መኖ ሩ ከተረጋገጠ እና ተራ ቁጥሮቹ በመስክ ላይ ካልተስተካከሉ አራሚው በተጨማሪ መጠይቅ ላይ «01» ወደ «12»፣ «02» ወደ «13» በመቀየር ማረም ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 301 <u>ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሠማርተው ነበርን ?</u>**

ይህ ጥያቄ ከዚህ በኋላ ለሚመጡ ጥያቄዎችና ክፍሎች መነሻና መሠረታዊ ጥያቄ ስለሆነ በጥንቃ ቄ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከላይ ከተዘረዘሩት ምርታማ ሥራዎች ቢያንስ በአ ንዱ ለተሰማራ የቤተሰብ አባል የሰራው <u>የስራ ዓይነት ተፅፎ</u> አዎን» የሚለው ኮድ 1 መሞላቱን በአንፃሩም በአንዱም እንኳን ሳልተሰማራ «የለም» የሚለው ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋ ል፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለሞቹ ውስጥ መታየት የሚገባቸው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ብቻ መሆን አለባ ቸው፡፡ በተጨማሪም«የለም» መልሰው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምዶች **ከ302-304** ሳይሞላላቸዉ ወደ ዓምድ 305 መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

**ዓምድ 302 : <u>የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሰሩዋቸው በሁሉም ምርታማ ሥራዎች ለስንት ሰዓት</u> <u>ሰርተዋል</u> ? የትርፍ ሰዓትን ያጠቃልላል፡፡**

ይህ ዓምድ በእያንዳንዱ ቀን የተሰራ የሥራ ሰዓት መጠን በተለየ ማስታወሻ ከተያዘ በኂላ ወደዚህ የተመዘገበበት ነው፡፡ እንደ ዓምድ 301 ሁሉ ይህም ዓምድ መሠረታዊ ነው፡፡ ምክንያቱም በሳምን ትውስጥ በሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ላይ ተመርኩዘን የቤተሰብ አባላትን ሥራ ያላቸው፣ ሥራ አ ጥ ወይም ከሁለቱም ውጭ ለመከፋፈል ስለሚረዳ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓምድ ያሉት መረጃዎች በ ጥንቃቄ መሞላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ክፍልፋይ ሰዓቶች ተጠጋግተው በሙሉ ቁጥር መጻፍ አለባቸው፡፡ «የሳምንቱ ምርታማ ስራ ሰዓት በሚለው ንዑስ አምድ ውስጥ

ተሞልቶ የመጣው ቁጥርና «97» እና ከዛ በላይ ከሆነ በዚሁ ዓምድ ሥር መታየት ያለበት ቁጥር «97» ነው።
ይህ ካልሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን ማስተካከል ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን በነዚህ ዓምዶች ኮድ 99 እንዳይሰፍር ይፈለጋል። ምክንያቱም በአንድ ቦታ እንኳን ኮድ 9 ካለ ድምሩ (በታቡሌሽን) ወቅት 99 ስለሚደረግ ነው።

**ዓምድ 303:-** **<u>ባለፉት 7 ቀናት ለዋነኛ ስራዎ ምን ያህል ሰዓት አዉለዋል?</u>**

**ይህ አምድ የአምድ 302 ንዑስ ክፍል ነዉ። ምክንያቱም በዚህ አምድ የሚሞለዉ ቁጥር ከአምድ 302 መብለጥ የለበትም። በዚህ አምድ የሚሞለዉ ለዋነኛ ስራዎ ማለትም በአምድ 302 ከተመዘጋበዉ ከጠቅላለዉ ሰዓቶች ለዋነኛ ስራዎ የወሰደዉን ረዥሙን ሰዓት ነዉ። በዚህ አምድ የሚታየዉ ቁጥር ከአምድ 302 ማነስ ወይም እኩል መሆኑን ማራጋጋጥ ያሻል።**

**ዓምድ 304:-** **<u>ባለፉት 7 ቀናት ለተጨማሪ ስራዎ/ችዎ ምን ያህል ሰዓት አዉለዋል?</u>**

**በዚህ አምድ የሚሞለዉ ቁጥር ከአምድ 302 መብለጥ የለበትም። በዚህ አምድ የሚሞለዉ ለተጨማሪ ስራዎ/ችዎ ማለትም በአምድ 302 ከተመዘጋበዉ ከጠቅላለዉ ሰዓቶች ለተጨማሪ ስራዎ/ችዎ የወሰደዉን ሰዓት/ቶች ነዉ/ናቸዉ። በዚህ አምድ የሚታየዉ ቁጥር ከአምድ 303 ሊበልጥ ወይም እኩል ወይም ሊያንስ ይችላል አንጅ ከአምድ 302 ሊበልጥ አይችልም። ተጨማሪ ስራ እያላቸዉ ላልሰሩ ኮድ :00፡ ሲሞላ ኮድ:98፡ ተጨማሪ ስራ ለሌላቸዉ ይሆናል።**

**ዓምድ 305:-** **<u>ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ስራ የሰሩት የስራ ሰዓት ድምር ስንት ነው?</u>**

ይህ አምድ በአምድ 302 ላይ የተመሠረተ ሲሆን
ለዚህ ጥያቄ በመጠይቁ ላይ የቀረቡት አማራጮች 2 ሲሆኑ እነዚህም ኮድ2 4 ሰዓትና በላይ፤ ኮድ 1. ከ4 ሰዓት በታች ወይም 302ን ላልተጠየቁ የሚሉ ናቸው። ስለዚህ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ኮድ «1» ወይም ኮድ «2» ብቻ መሆን አለበት።
ከዚያም ከ4 ሰዓት በላይ ሰርተው ኮድ «2» የተሞላላቸው የሚከተሉትን ሁለት አምዶች ማለትም አምድ 306 እና አምድ307ን ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 308 ማለፋቸውን ማረጋገተ ያስፈልጋል።በአምድ 301 ኮድ 2 በመሞለቱ ምክንያት አምድ 302 ከልተሞላ በአምድ 305 ኮድ 1 መሞለቱ መራጋጋጥ አለበት።

**ዓምድ 306:-** **<u>ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?</u>**

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ላይ መረጃ ተሞልቶ የሚመጣው በዓምድ 301 ኮድ 2 ለተሞላላቸው እና በዓምድ 301 ኮድ 1 የተሞላላቸው ቢሆንም፣በአጠቃላይ በሳምንት ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ለሆነ በዓምድ 305 ኮድ «1» ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ እና ምንም ስራ ላልሠሩ የቤተሰብ አባላት ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በሥራ ላይ ካልተሠማሩ አዎን የሚለው ከኮድ «1-3» ሲሞላ ነገር ግን ሥራ ሳይኖራቸው ከሆነ የለም የሚለው ኮድ «4» ሊሞላላቸው ይገባል። በመጨረሻም በዚህ ዓምድ የለም ብለው ኮድ «4» የተሞላላቸው ግለሰቦች እስከ ዓምድ

401 ድረስ ምንም መረጃ ሳይሞላላቸው በቀጥታ ወደ ዓምድ 401 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

**ዓምድ 307 - <u>ባለፉት 7 ቀናት ሥራዎን ያልሰሩበት ዋና ምክንያት ምንድነው?</u>**

በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ የቤተሰብ አባላት በዓምድ 306 ኮድ «1-3» የተሞላላቸው ማለትም ሥራ እያላቸው በሥራ ላይ ያልተሠማሩ ናቸው። ባለፉት 7 ቀናት ውስ ጥ ከሥራ ሊያስቀሯቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ 5 አማራጭ መልሶች በዚህ ዓምድ ውስጥ ተዘርዝረዋል። ስለሆነም ምክንያትና በዓምድ የተሰጠው ከሥሩ በሚገኘው ካርድ ኮለም የተሞ ላው ኮድ ትክክል መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል። ከተዘረዘሩት የተለየ መልስ ተሰጥቶ ከሆነ ኮድ 6 ተሞልቶ መገለፁን ማየት ያሻል። የካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-6 ውጭ መሆን የለባቸውም። በመጨረሻም በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉም ቀጣዩን ዓምድ 308 መጠየቃቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**ዓምድ 308 - 311 ፡- <u>የሥራ ዓይነት፣ የድርጅት ዋና ምርት/ አገልግሎት፣ የቅጥር ሁኔታ/Employment Status/ እና የሥራ ቦታ</u>**

እነዚህ ዓምዶች የሚሞሉት በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት የሥራ ሰዓት መጠን ቢያንስ 4 ሰ ዓት ለሆነ ማለትም በዓምድ 305 ኮድ «2» ለተሞላላቸው ግለሰቦች፣ባለፉት 7 ቀናት ስራ እያላቸው ላልሰሩ
እና ምንም እንኳን በጥናቱ ሳምንት በአጠቃላይ የሠሩት ሥራ ሰዓት መጠን ከ4 ሰዓት በታች ቢሆንም ሥራ እያላቸው ላልሠሩ ግለሰቦች ጭምር ነው። ስለዚህ በዓምድ 305 ኮድ 2 ወይም በዓምድ 306 ላይ ከኮድ1-3 የተሞላላቸው በዚህ ክፍል ከዓምድ308-320 ድረስ መረጃዎች ተሞልተውላቸው መምጣታቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

**ዓምድ 308፡ <u>ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የዋነኛ ስራዎ ዓይነት ምንድነው ?</u>**

በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸወ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ያልነበሩ ግለሰቦች (በዓምድ 306 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዚህ ዓምድ የዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ተሞልቶ መጥቷል። ለዚህ ዋነኛ የሥራ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ "የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ምደባና ኮድ ዝርዝር" ተብሎ ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮዱ የተሞላ ቢሆንም የኤዲተሮች ዋና ሥራ የሚሆነው የኮዱን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ነው። የዋነኛ የሥራ ዓይነት ከኮድ ዝርዝር መጽሐፍ ውስጥ መጣጣም ካልቻለ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት ቢቻል ተቀራራቢ የሆነውን የሥራ ዓይነት ኮድ መሙላት ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ በመስክ የተሞላው የሥራ ዓይነት ግልፅና በቀላሉ የማይነበብ ለመረዳትም አስቸጋሪ ከሆነ ኢዲተሩ በእርጋታና በትዕግስት መረጃ ሰብሳቢው የሞላውን ማጣራት ይኖርበታል። ከዚህም በተጨማሪ ከሥራ ዓይነት ኮድ ዝርዝሩ ጋር ለማገናኘት ሲሞክር በቅድሚያ የተጠቀሰው የሥራ ዓይነት በየትኛው ዋና ክፍል እንደሆነ መለየት ከዚያም በዋና ክፍሉ ሥር ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች ለየትኛው እንደሚቀርብ አመዛዝኖ ኮድ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም ለመወሰን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በመጠራጠር ኮድ ከማድረግ መቆጠብና ተቆጣጣሪውን በማማከር

ትክክለኛውን ኮድ መስጠት ይገባል፡፡ ስለዚህ በኮድ ዝርዝሩ ከተሰጠው የማይጣጣም ሆኖ ከተገኘ ከተቆጣጣሪውና ከአሰሪው ክፍል ጋር ተነጋግሮ አዲስ ኮድ መስጠት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

**ዓምድ 309:-** ***<u>ይህንን ሥራ የሚሰሩት የት ነው ?</u>***

*በዚህ ጥያቄ አያሌ ሰዎች ሊሠሩበት ይችላሉ የተባሉት ዋና ዋና የሥራ ቦታዎች ከኮድ 00 እስከ 09 ድረስ የተሞላ ሲሆን፣ ከነዚህ ኮዶች ውጭ ከተሞላ ግን ስህተት ስለሆነ መስተካከል ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ሌላ ተብሎ ኮድ 09 የተሰጠው ካለ ከ00-08 ካለው ውስጥ የሚካተት ከሆነ በዚሁ ኮድ እንዲካተት ማድረግ ያሻል፡፡*

**ዓምድ 310** ***<u>በዋነኛነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው?</u>***

*በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ ሳምንት በሥራ ላይ ለነበሩና ሥራ ኖሯቸው በጥናቱ ሳምንት ሥራ ላይ ላልነበሩ ግለሰቦች በዚህ ዓምድ በዋነኝነት የሚሰሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት /ኢንዱሰትሪ/ ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ለዚህ የኢንዱስትሪ ዓይነት ተገቢ የሆነው የመለያ ኮድ ከ" <u>የሥራ ዓይነትና የድርጅት ዋና ምርት ወይም አገልግሎት</u> <u>ኮድ ዝርዝር</u>" ተብሎ የተዘጋጀው መጽሐፍ በመውሰድ ኮድ ተሞልቷል፡፡ኤዲተሩ ይህ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ የኢንዱስትሪ ነገር ግን በመስክ ላይ የተሞላው የድርጅት ምርት/አገልግሎት ሳይሆን የድርጅቱ ስም ወይም ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ከተቆጣጣሪው ጋር በመመካከር የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት ምን እንደሆነ ለማወቅ የተለያዩ ግንዛቤዎችንና ሁኔታዎችን በመውሰድ ለመሙላት ይሞከራል፡፡*

**ዓምድ 311** ***የ<u>ዋነኛ ሥራዎ የቅጥር</u>*** **<u>(Employment Status)</u>** ***<u>ሁኔታ ምንድነው ?</u>***

*ለዓምዱ የተሰጠው ክፍት ቦታ ተሞልቶ የመጣው የቅጥር ሁኔታ ከሥር በካርድ ኮለሙ ከተሞላው ኮድ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከጥያቄው ሥር የተዘረዘሩት 12 አማራጭ መልሶች ከኮድ 01-12 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሳይሞላ መምጣቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከኮድ 08-12 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን ዓምዶች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 318 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ሲገባ ኮድ 07 የተሞላላቸው ደግሞ ወደ ዓምድ 319 መሽጋገራቸውን ማጣራት ተገቢ ይሆናል፡፡ የአማራጭ መልሶች ዝርዝር መጠይቁ ላይ ከጥያቄው ሥር ቀርበዋል፡፡*

**ዓምድ 312:-** ***<u>የዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ዓይነት ምንድነው?</u>***

ለዚህ ዓምድ አምስት አማራጭ ኮዶች (ከጥያቄው ሥር) ቀርበዋል፡፡ ስለሆነም ከላይ የቅጥር ዓይነቱ፣ ከሥር በሚገኘው ካርድ ኮለም ደግሞ ተስማሚው ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ1-5 ውጭ መሆን የለባቸውም፡፡

**ዓምድ 313-317፡-   /ከቅጥር ስራ የተገኘ ክፍያ/ በዓምድ 311 ከኮድ 01 - 06**

**ዓምድ 313-  ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት?**

በዚህ ዓምድ ጥያቄው የተጠየቀላቸው ከላይ በዓምድ 311 ከኮድ 01-06 ለተሞላላቸው ስለሆነ ከነዚህ ኮዶች ውጭ (07-12) የተሞላላቸው ግን ይህንን ዓምድ አለመጠየቃቸውንና ከተጠየቁም በጥንቃቄ ታርሞ ተገቢው ኮድ እንዲሞላላቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት 3 አማራጭ መልሶች የተዘጋጁት 3 ኮዶች በመሆናቸው ከነዚህ ውጭ በተከታታይነት ተሞልተው ከመጡት ሌሎች መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ማስተካከል ተገቢ ይሆናል፡፡ አማራጭ መልሶቹ ከጥያቄው ስር ስለተዘረዘሩ የተሞላውን ኮድ ተመሳሳይነትም ማገናዘብ ይገባል፡፡

**ዓምድ 314፡-  ለዋናው ሥራዎ የአከፋፈል ጊዜ እንዴት ነው ?**

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 311 ከኮድ 01-06 ተሞልቶላቸው ከሆነ ብቻ ነው የሚጠየቁት ስለሆነም እነዚህ ግለሰቦች ብቻ መጠየቃቸው መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ለተሰጡት ሰባት አማራጭ መልሶች ከ1-7 ኮድ ተሰጥቶአቸው ከጥያቄው ስር ተዘርዝረዋል፡፡ ስለሆነም፣ በዓምዱ ስር በጽሁፍ የተገለፀው የአከፋፈል ጊዜና በካርድ ኮለሙ የተሞላው ኮድ መጣጣማቸው ይረጋገጣል፡፡ በመጨረሻም ከኮድ 5-7 የተሞላላቸው ቀጣዮቹን /ሁለት ጥያቄዎች ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 317 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 315፡-  በገለፁልኝ የአከፋፈል መሠረት ባለፈው ወር ለስንት የአከፋፈል ጊዜያት ሠርተዋል?**

በዚህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 311 ከኮድ 01-06 የተሞላላቸው ብቻ መጠየቃቸው ይረጋገጣል፡፡ ጥያቄው በዓምድ 314 በተገለፀው የአከፋፈል ጊዜ መሠረት ለምን ያህል ጊዜ እየተከፈላቸው መሥራታቸውን ተጠይቀው ተሞልቷል ፡፡ በዚህ መሠረት በዓምዱ ሦስት ካርድ ኮለም ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም በዓምድ 314 በየቀኑ ብለው ኮድ "2" የመለሱ በዚህ ዓምድ (በዓምድ 315) ላይ ከ30፣ በየሳምንቱ ኮድ "3" ለተሞላለት ደግሞ ከ4 እንዲሁም በየ15 ቀኑ ብሎ ኮድ "4" ለተሞላላት ከ2 አለመብለጡን በአትኩሮት ማየት ያስፈልጋል፡፡

**ዓምድ 316፡-  በዓምድ 314 በገለፁልኝ አከፋፈል መሠረት ለመጨረሻ ጊዜ ምን ያህል ተከፈልዎት?**

ይህ ጥያቄ ግለሰቦች በዓምድ 314 ለገለፁት የአከፋፈል ሁኔታ በመጨረሻው ክፍያቸው ያገኙት የብር መጠን ተሞልቶ መጥቷል፡፡ ለዚህም አራት ካርድ ኮለሞች የተዘጋጁ ስለሆነ በዚሁ መፃፊያ በተዘጋጁት ካርድ ኮለሞች ቁጥሮች ከቀኝ ወደ ግራ መሞላቱን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ማለት የብሩ መጠን በካርድ ኮለሙ ሲፃፍ መጀመር የሚኖርበት ከቀኝ ይሆናል፡፡ ስለዚህ "30 ብር" ያለ መልስ ሰጪ ብሩ በዓምዱ ሲሰፍር "0" "0" "3" "0" መሆን ይኖርበታል፡፡ እዚህ ላይ ከብር "9997" እና በላይ ለሚከፈላቸው "9997" ብቻ መሞላት ይኖርበታል፡፡

**ዓምድ 317፡- በዋነኛነት ለሰሩት ሥራ ባለፈው አንድ ወር ውስጥ በጠቅላላው ምን ያህል ተከፈለዎት ?**

ይህ ጥያቄ የመልስ ሰጪዎቹ ከቅጥር ሥራ የተገኘ የወር ክፍያ መጠን የተጠየቀበት ሲሆን በዓምድ 316 ከተሞላው ጋር ሊነፃፀር ይችላል፡፡ ይኸውም የአከፋፈል ጊዜው በሣምንት/አስራ አምስት ቀን የሆነ ሠራተኛ/ቅጥረኛ በዓምድ 316 ያስመዘገበው የገንዘብ መጠን ከዓምድ 317 ማነስ ወይም እኩል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን በተመሳሳይ መልኩም በካርድ ኮለሙ ውስጥ የቁጥሮቹ አፃፃፍ ከላይ በተገለፀው መሠረት ከቀኝ በመጀመር ይሆናል፡፡ የወር ገቢያቸው ከብር "9997" እና በላይ ለሆነ የሚፃፈው ይኸው "9997" ይሆናል፡፡

**ዓምድ 318፡- ድርጅቱ/የሥራ መስኩ/**

በግል የግብርና ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦች ተሞልተው የመጡት መረጃዎች በሙሉ ኮድ 1 ማለትም አዎን የሚል መልስ እንደተሞላላቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ዓምዶች ተሞልተው መምጣት የሚገባቸው ለሁሉም ግለሰቦች ሳይሆን በዓምድ 311 የቅጥር ሁኔታዎች ኮድ 03፣ 06፣ 08፣09፣10፣11 ወይም 12 ለሆኑ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ከነዚህ ግለሰቦች ውጭ ለሌሎችም መረጃ ተሞለቶ ከመጣ ስህተት ስለሆነ ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡

**A. አሥር ወይም በላይ የሥራው ተከፋይ ሠራተኞች አሉት?**

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 3 አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡ ስለሆነም በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ኮዶች ኮድ «1» ማለት «10ና በላይ» ወይም ኮድ «2» ማለትም ከ10 በታች ወይም የለም የሚሉት ወይም ኮድ 3 ማለትም
አላውቅም መሆን አለባቸው፡ በተጨማሪም ከላይ ለተጻፉት ቃላት
ከሥር በካርድ ኮለሙ የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ያሻል፡፡

**B. የተሟላ የሒሳብ መዝገብ አለው?**

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 3 አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ በካርድ ኮለም ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ አለሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**C. ፈቃድ አለው ?**

ለጥያቄውም የቀረቡት አማራጭ መልሶች 3 ብቻ ስለሆኑ ከነዚህ ኮዶች ማለትም ኮድ 1፣ 2 ወይም 3 ውጭ በካርድ ኮለሙ አለመሞላቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

***ዓምድ 319:-*** ***ሥራ ላይ ለነበሩ***

***ባለፈው ሳምንት ተጨማሪ ሰዓት ለመሥራት ዝግጁነትና ፍላጎት ነበረዎት? /ከ4 ሰዓት በላይ ለሰሩ- በዓምድ 305 ኮድ 2 ለተሞላላቸው/***

***ሥራ ላይ ላልነበሩ***

***ባለፈው ሳምንት ለመስራት ዝግጁነትና ፍላጎት ነበረዎት? /ሥራ እያላቸው ላልሰሩ-/ በዓምድ 306 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው/***

*ይህ ጥያቄ በዓምድ 305 ኮድ 2 ለተሞላላቸው እና በዓምድ 306 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው ሁሉ ይጠየቅላቸዋል፡፡በተጨማሪም ለጥያቄው የተሰጡት አማራጭ መልሶች አዎን ኮድ 1 እና የለም፣ ኮድ 2 ስለሆኑ ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ ሌላ አለመሞላቱን መታየት አለበት፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ኮድ 1 የተሞላላቸው ቀጣዩን ጥያቄ ሲጠየቁ ኮድ 2 የተሞላላቸው ከሆነ ወደ ክፍል 5 ይሸጋገራሉ፡፡ ይህንንም ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡*

***ዓምድ 320*** ***ተጨማሪውን ሰዓት በምን ዓይነት ሥራ መሰማራት ይፈልጉ ነበር?***

*በዚህ ዓምድ መረጃ ተሞልቶ ሊመጣላቸው የሚገባ ግለሰቦች ዓምድ 319 አዎን ብለው ኮድ «1» የተሞላላቸው ብቻ ናቸው፡ ስለሆነም በዓምድ 319 ኮድ «2» የተሞላላቸው በዚህ ዓምድ ላይ መ ረጃ ተሞልቶላቸው ከመጣ ስህተት ሊሆን፣ ስለሚችል ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ በማሳየት መረጃውን መሰረዝ ያስፈልጋል፡፡ የቀረቡት (ከጥያቄው ሥር) አማራጭ መልሶችም 3 ብቻ ስለሆኑ በካርድ ኮለሙ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከ1-3 ውጭ መሆን እንደሌለበትና በተጨማሪም በዓምዱ ክፍት ቦታ ለተጻፉት ቃላት ከሥር የተሞሉት ኮዶች ተገቢ መሆናቸውን ማገናዘብ ይገባል፡፡*

# ክፍል 4፡- ሥራ አጥነትና የሥራ አጦች ባህሪይ

ዓምድ 202፡- ሙሉ ስም፡- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሙሉ ስም ከገጽ 1 ዓምድ 11 በትክክል መወራረሱን ማገናዘብ ይገባል፡፡

ዓምድ 201፡- የመሥመር ቁጥር፡- ቀድሞ የተሞላ ስለሆነ ምንም አይነካም፡፡

## ዓምድ 401 - 410፡- ሥራ አጥነት

## ዓምድ 401- ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?

መጀመሪያ በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የሚሞላላቸው በክፍል 3 ዓምድ 306 ላይ የለም መልሰው ኮድ «4» ለተሞላላቸው ግለሰቦች መሆኑን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ለሌሎች ግለሰቦች ግን ካርድ ኮለሞቹ በሠረዝ «-» ይታለፋሉ፡፡

ለዚህ ዓምድ የቀረቡት አማራጮች አዎን ብለው ለመለሱ ኮድ «1» እና የለም ላሉ ኮድ «2» ስለሆኑ በተገቢው ካርድ ኮለም ከሁለቱ ኮዶች አንደኛው ብቻ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ከዚያም የለም ብለው ኮድ «2» የተሞላላቸው ዓምድ 402ን ተሻግረው ወደ ዓምድ 403 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ዓምድ 402፡- ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምን ጥረት አደረጉ?

ይህ ዓምድ የሚሞላው በዓምድ 401 ኮድ «1» ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርጌ ነበር ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ ከዓምዱ ግርጌም 8 አማራጭ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ኮዶች ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ግለሰቡ ያደረጉት ጥረት ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ደግሞ ተገቢው ኮድ ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ከዚያም በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ የተሞላላቸው ግለሰቦች ሁሉም ወደ ዓምድ 404 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያሻል፡፡

**ዓምድ 403:-** ለምንድነው ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 401 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ሥራ ለማግኘት ምንም ጥረት ላላደረጉ ግለሰቦች ብቻ ነው፡፡ ሥራ ለመሥራት ወይም ለማግኘት ጥረት ያላደረጉበት ምክንያት በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት 14 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር መሞላቱንና ተገቢው ኮድ ደግሞ በካርድ ኮለሞቹ መሞላቱን ማረጋገጥ ያሻል፡፡ የተሰጡት ኮዶች ከ01 - 14 ስለሆኑ በካርድ ኮለሞቹ ተሞልተው የመጡት ቁጥሮች ከነዚህ ውጭ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡

ዓምድ 404:- በሚቀጥለው 1 ወር ውስጥ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ቢያገኙ ይሰራሉ?

ለዚህ ጥያቄ አዎን ብለው የመለሱ ግለሰቦች ኮድ «1» የለም ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ «2» እንደተሞላላቸው በተጨማሪም በካርድ ኮለም ውስጥ መታየት የሚገባቸው ቁጥሮችም ከነዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚያም የለም ብለው መልሰው ኮድ «2» የተሞላላቸው ተከታዩን ዓምድ 405ን ዘለው ወደ ዓምድ 406 መሻገራቸውን ማየት ያስፈልጋል::

ዓምድ 405:- በአቅምዎ ተቀጥረው ሊሰሩት የሚችሉት ስራ ቢገኝልዎት ወይም በግል ሥራ ለመስማራት አስፈላጊ ነገሮች ቢሟሉ ስራ ለመጀመር ዝግጁ ነዎት? ከሆነ የት?

በዚህ ዓምድ ለቀረበው ጥያቄ 6 አማራጭ ሊሆኑ የሚችሉ መልሶች ከኮድ 1 - 6 የተሰጡ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ ተሞልቶ የመጣው ኮድም ከነዚህ ቁጥሮች ውጭ አለመሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው:: ከዚያም ኮድ 2፣ 3፣ 4፣ 5 ወይም ኮድ 6 የተሞላላቸው ግለሰቦች ተከታዮቹን አንድ ዓምድ ዘለው ወደ ዓምድ 407 መሻገራቸውን ማየት ይገባል፡

ዓምድ 406:- ለምንድነው ሥራ ቢያገኙ የማይሰሩት?

በዓምድ 405 ላይ ሥራ ቢገኝላቸው ለመሥራት ዝግጁ አይደለሁም ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ግለሰቦች በሙሉ በዚህ ዓምድ ለምን ሥራ ቢያገኙ እንደማይሠሩ በዓምዱ ሥር ከተዘረዘሩት አማራጮች አንዱና ዋነኛው ምክንያት ይሞላል:: ከተዘረዘሩት 8 አማራጭ መልሶች ውስጥ አንዱ በዓምዱ ሥር ተጽፎ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ላይ መሞላት አለበት:: ስለዚህ ካርድ ኮለሙ ውስጥ ተሞልቶ የመጣው ቁጥር ከ0-8 ካሉት ውጭ አለመሆኑና ኮዱም ለምክንያ ተገቢው መሆኑን ማረጋገጥ ያሻል:: ከዚያም ከኮድ 0-8 የተሞላላቸው በሙሉ ወደ ዓምድ 501 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

## ዓምድ 407:- የሚፈልጉት ሥራ ምን ዓይነት ነው?

በመጀመሪያ ይህ ዓምድ ተሞልቶ የመጣው በዓምድ 405 ላይ ከኮድ 2-6 የተሞላላቸው ግለሰቦች ብቻ መሆኑን ማገናዘብ ያስፈልጋል:: በዓምዱም ተሞልቶ የመጣው መረጃ ከጥያቄው ሥር ከተዘረዘሩት 5 አማራጭ መልሶች ውጭ አለመሆኑንና ለመልሱም ተገቢው ኮድ በኮድ መሙያ ቦታው ላይ ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ያስፈልጋል:: ከዚያም ከኮድ 2-5 የተሞላላቸው በሙሉ ተከታዩን ዓምድ ዘለው ወደ ዓምድ 409 መሻገራቸውን ማረጋገጥ ይገባል::

ዓምድ 408:- የግል ሥራ /የራስን ድርጅት ለማቋቋም የገጠሞት/የሚገጥሞት ችግር አለ? ፣ ካለ ምንድነው?

ይህ ዓምድ የሚሞላላቸው በዓምድ 407 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው ማለትም የራሴን ድርጅት ማቋቋም እፈልጋለሁ ላሉ ግለሰቦች ብቻ ነው:: የገጠሟቸው ወይም ሊገጥሟቸው ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱ ችግሮች ከመጠይቁ ግርጌ ከኮድ 00-10 የተዘረዘሩ ስለሆነ ከነዚህ ምክንያቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ከላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ተሞልቶ መምጣቱንና ተገቢው ኮድም ከሥር ባለው ካርድ ኮለም ውስጥ ተሞልቶ መምጣቱን ማገናዘብ ያሻል:: ተሞልተው የመጡት ኮዶች ከ00-10 ካሉት ውጭ አለመሆኑን በጥንቃቄ ማየት ይገባል::

**ዓምድ 409:** **<u>ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያውቃሉ ?</u>**

ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች ከዚህ በፊት በቅጥር ወይም በግል ሥራ ሠርተው ያወቁ እንደሆነ በዚህ ዓምድ ይጠየቃሉ፡፡ ከዚህ በፊት በቅጥር ሥራ ተሠማርተው ለሚያውቁ አዎን በቅጥር ኮድ 2፣ አዎን ለቤተሰብ
ኮድ 3 ወይም አዎን በግል ሥራ ኮድ 4፣ በቅጥር ወይም በግል ሥራ ተሠማርተው ለማያውቁ ደግሞ የለም የሚለው ኮድ 1 ተሞልተው መምጣት አለባቸው፡፡ ከኮድ 1-4 ውጪ ተሞልቶ መምጣት የለበትም፡፡

**ዓምድ 410-** **<u>ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ ቆይተዋል?/በወራት ይገለፅ/</u>**

በዚህ ዓምድ ሥራ አጥ የሆኑ ግለሰቦች በሙሉ ለምን ያህል ወራት ያለ ሥራ እንደቆዩ የሚጠየቁበ ት ሲሆን መረጃው በሙሉ ወራት ተሞልቶ መምጣቱን ማየት ተገቢ ነው፡፡ በካርድ ኮለሙ የተሞላ ው ቁጥር ከ97 በላይ ከሆነ ተሠርዞ ኮድ «97» ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ምንም ሳይሞላ በሁለተኛው ንዑስ ዓምድ ብቻ ተሞልቶ ከመጣ የመጀመሪያው ንዑስ ዓምድ ላይ 0 መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

## ክፍል 5 ፡ ያለፉት 6 ወራት የሥራ ሁኔታ

ዓምድ 501፡- ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን በምርታማ ሥራ ማለትም ተቀጥረው በክፍያ ወይም ትርፍ ለማግኘት ወይም ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር?

ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች "አዎን" እና "የለም" ሲሆኑ በዚህ መሠረት በዓምዱ ስር ስራ ሠርተወ ለነበሩ የሠሩት የሥራ ዝርዝር ከተፃፈ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 መፃፉንና ቀጣዩን ዓምድ 502 ሳይጠየቁ ወደ ዓምድ 503 መተላለፋቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል። ይህ ሁሉ ከተረጋገጠ በኋላ " የለም" ብለው ኮድ 2 የተሞላላቸው ቀጣዩን ዓምድ 502 መጠያቀቸዉን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል።

ዓምድ 502 ባለፉት 6 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ምርታማ ሥራ ለመሰራት ዝግጁ ነበሩ ?

**ይህን አምድ የሚጠየቁት በአምድ 501 ኮድ 2 የተሞላላቸዉ መሆናቸዉን መራጋጋጥ ያሻል። ለዚህ ጥያቄ እንደ አማራጭ የተሰጡት መልሶች አዎን እና የለም ሲሆኑ፣ በዚሁ መሠረት በዓምድ ስር ስራ ለመስራት ዝግጁ የነበሩት አዎን ብሎ ኮድ 1 መሞላቱንና የለም ያሉት ደግሞ ኮድ 2 መሞላቱን ማረጋገጥ ያሰፈልጋል።**

ዓምድ 503: ባለፋት 6 ወራት ለስንት ሳምንታት በሥራ ላይ ነበሩ ?

ይህ ጥያቄ ተጠያቂዎች ባለፉት 6 ወራት ምን ያህል ሳምንታት በሥራ ላይ እንደነበሩ ለማወቅ በሳምንታት ተከፋፍሎ ተጠይቋል። ስለሆነም በእያንዳንዱ ወር አንፃር "ሥራ ላይ" የነበሩበት ጊዜ ተጠይቆላቸው በዚህ ዓምድ ተሞልቷል። እናም ይህ ዓምድ እና ቀጣይ ሁለት ዓምዶች ላይ የተሞላው የሳምንታት ብዛት ተደምረው ከ24 የማይበልጡ/የማያንሱ መሆናቸው መጣራት አለበት።

ዓምድ 504: ባለፋት 6 ወራት ለስንት ሣምንታት ሥራ አጥ ነበሩ?

**በዚህ ዓምድ ተጠያቂዎች ባለፋት 6 ወራት ለምን ያህል ሳምንታት ያለሥራ ሆነው ስራ ለመሰራት ዝግጁ እንደነበሩ ተጠይቀዋል። እነዚህ ግለሰቦች በዓምድ 502 ላይ ኮድ 1 የተሞላላቸው መሆኑን ማጣራት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በዓምድ 410 ከተሞላው የወራት ጊዜ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማየት ያሻል። ለምሳሌ በዓምድ 410 ላይ አንድ ግለሰብ ለ6 ወራት ያህል ያለስራ እንደቆየ የተሞላለት ከሆነ በዚህም ዓምድ ላይ የግድ 24 ሳምንታት መሞላት ይገባዋል። ካልሆነ ግን ስህተት ስለሆነ ተጨማሪ ማነፃፀር የሚያስፈልጋቸውን ዓምዶች በማየት ማረም ስለሚገባ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን መፍትሔ መሻት ይገባል። በሌላ መልኩ ደግሞ በዓምድ 502 ኮድ 2 ተሞልቶ በዓምድ 505 ደግሞ 24 የተሞላ ከሆነ ይህ ዓምድ በ --- /ሠረዝ የሚታለፉ ይሆናል።**

**ዓምድ 505:-** **ባለፉት 6 ወራት ለስንት ሳምንታት ሥራ ለመሥራት አልቻሉም /ዝግጁ አልነበሩም?**

ግለሰቦች ለዚህ ጥያቄ የመለሱት የሳምንታት ብዛት በዓምድ 503 እና 504 ከተሞላው ጋር ተደምሮ 24 መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህ ሆኖ ካልተገኘ ከሶስቱ ዓምዶች በአንዱ ብቻ ችግሩ ተከስቶ ሊሆን ስለሚችል ሌሎች ዓምዶች ጋር በማዛመድ ለማረም የሚቻል ከሆነ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ለማየት መሞከር ያስፈልጋል::

**ዓምድ 506:-** **መረጃ ሰብሳቢ በዓምድ 505 ያለውን ጠቅላላ የሳምንታት ድምር በማየት ማረጋገጥ**

በዚህ ዓምድ ላይ መረጃ ሰብሳቢው በዓምድ 505 የተሞላውን የሳምንታት ብዛት በማየት ያረጋገጠ ሲሆን፣ በዓምዱ /505/ የተሞላው 12 ሳምንታትና በላይ ከሆነ ኮድ 1 እና ከ12 ሳምንታት በታች ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 የተሞላ መሆኑንና ጥያቄዉ መብ ቃቱን ማየት ያሻል::

**ዓምድ 507** **ባለፉት 6 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ያልሰሩበት ወይንም ለመስራት ዝግጁ ያልነበሩበት ምክንያት ምንድን ነበር ?**

ይህ ዓምድ ለመልስ ሰጪዎች ስራ ያልሰሩበትን ምክንያት ከተሰጡት አማራጮች ከ1-8 የመለሱ ሲሆን ከነዚህ ቁጥሮች/ኮዶች/ ውጭ ሌላ ከተሞላ መስተካከል ያስፈልገዋል:: በመሆኑም ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት በዓምዱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ተገልጾ ተገቢው ኮድ ደግሞ ከስር ባለው ካርድ ኮለም ተሞልቶ መምጣቱን ማረጋገጥ ይገባል::

## ክፍል 6:- ከአምድ 601-612 ዕድሜያቸው ከ5-17 ዓመት ለሆናቸው ልጆች የሚጠየቅ ነው::

ዓምድ 601:- በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተልክ/ሽ ነው?

በዚህ ዓምድ እድሜያቸው ከ5 አመት እስከ 17 አመት ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት መከታተላቸውንና አለመከታተላቸውን ይጠየቃሉ:: ስለሆነም፣ በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተሉ ከሆነ ኮድ 1 ተሞልቶ ቀጣዩ ዓምድ የሚጠየቅላቸው ሲሆን፣ ትምህርት አልተከታተልንም ላሉት ኮድ 2 ተሞልቶላቸው በቀጥታ ወደ ዓምድ 603 ማለፋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 602:- ምን ዓይነት ትምህርት እየተከታተልክ/ሽ ነው?

በዚህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው በዓምድ 601 አዎን ብለው ኮድ 1 ለመለሱትና በያዝነው ዓመት ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙት ሲሆን ፣ መልሱ በጽሁፍ ይፃፍና በንዑስ ዓምድ ደግሞ ኮዱ 1 መሞላቱን፣ ትምህርቱ ግን የሙያ /ቴክኒክ ለሆኑት ደግሞ መልሱ በጽሑፍ ተገልጾ ኮድ 2 የሚሞላ ሲሆን፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ለሚከታተሉ ልጆች ኮድ 3 መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

***ዓምድ 603:- ትምህርት ያልተከታተልክበት/ሽበት ምክንያት ምንድነው?***

***በዚህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው በዓምድ 601 ኮድ 2 ለመለሱት ማለትም በያዝነው አመት ትምህርት ያልተከታተሉበትን ምክንያት ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ተቀራራቢ ከሆኑት ዋንኛ የሆነውን ምክንያትን ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: አማራጭ መልሶችም እንደሚከተሉት ቀርበዋል::***

1. በአቅራቢያ ት/ቤት ባለመኖሩ፣
2. ቤተሰቤ ለት/ቤት የመከፍለው ገንዘብ ስለሌለው
3. ትምህር ለመማር ፍላጎት ስለሌለኝ
4. በትምህርት ስለወደቅሁ
5. አስተማሪዎችን ስለምፈራ
6. በህመም (በአካል ጉዳት)
7. በቤት ውስጥ ሥራ ቤተሰቦቼን ስለምረዳ
8. እራሴን ለመርዳት ስል ስለምሠራ
9. ለቤተሰቤ ገቢ ለማስገኝት ስል ስለምሠራ
10. ቤተሰቦቼ ትምህርት እንድከታተል ስለማይፈቅዱልኝ
11. በጋብቻ ምክንያት
12. በመፈናቀል (በጦርነት፣በድርቅ)
13. በቤተሰብ ዝውውር
14. በቤተሰብ መበተን (በፍች፣በሞት)
15. ሌላ ይገለጽ::

***ዓምድ 604:- ሥራ ሠርተሀ/ሽ ታውቂያለሽ?***

***በዚህ ዓምድ እድሜጣቸው ከ 5-17 ዓመት የሆናቸው ልጆች የሚመለከት ሲሆን ምርታማ ሆነ ምርታማ ያልሆነ ስራዎች ማለትም የቤት ውስጥ ስራ የመስራት ልምዳቸውን ለማወቅ ነው:: ሠርቻለሁ ላሉት ኮድ 1 ይሞላቸውና ወደቀጣዩ ዓምድ መሸጋገራቸው እና ማኛ ውንም ዓይነት ስራ አልሠራሁም ብለው ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶላቸው ጥያቄው የሚያቃ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::***

***ዓምድ 605:- በተሠማራበት/ሽበት ስራ የአካል/የአዕምሮ ችግር አጋጥሞሀል/ሻል?***

***በዚህ ዓምድ የሚጠየቅላቸው ልጆች ስራ እየሠሩ ወይም በሥራ ላይ፣ (በሥራ ቦታ) የደረሰ የአካል ወይም የአዕምሮ ችግር ወይም በሰራው ምክንያት ህመም/የአካል ጉዳት/ ደርሶባቸው እንደሆነ ለማወቅ ሲሆን፣ ደርሶ ከሆነ ኮድ 1 ይመዘገባል:: ካልደረሰ ደግሞ ኮድ 2 ይመዘገብና ወደ ዓምድ 607 መታለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::***

***ዓምድ 606:- የአስከተለው የአካል/የአዕምሮ ችግር ካለ ምን ዓይነት ነው?***

በዚህ ዓምድ የሚጠየቁላቸው ባከናወኗቸውም ሆነ አሁን እየሠሩ ባሏቸው ሥራዎች ምክንያት ከደረሱባቸው የአካል/የአዕምሮ ጉዳቶች መካከል ዋንኛው የአካል ጉዳት/ህመም በተሰጠው ክፍት ቦታ መፃፋቸውንና ለኮዱ በተሰጠው ዓምድ ሥር መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: አማራጭ መልሶችም የሚከተሉት ናቸው::

1. አጠቃላይ በሽታ
   ለምሳሌ
   እንደትኩሳት፣ ብርድ.ወዘተ
2. የአይን ህመም
3. የጆሮ ህመም
4. የቆዳ ህመም
5. የመተንፈስ ችግር
6. የማጅራት በሽታ
7. የወገብ በሽታ
8. ደም ማነስ
9. የአካል መላጥና /መቀጥቀጥ/
10. የአካል መቃጠል
11. የእጅ/የእግር መቆረጥ
12. የእጅ/የእግር/መጎረድ
13. የአካል መወጋት
14. ውልቃት
15. የአካል መሰበር
16. የስር መዞር
17. የዓይን ጉዳት
18. የጆሮ ጉዳት
19. መታፈን
20. የመስመጥ ችግር
21. ሌላ በሽታ/ይገለጽ
22. ሌላ ጉዳት/ይገለጽ/

ዓምድ 607:- በሥራ ላይ እያለ/ች የአደጋ/ጉዳት/መከላከያዎች ይጠቀማል/ ትጠቀሚለሽ?

በዚህ ዓምድ ለማወቅ የተፈለገው ሥራ ላይ ለተሠማሩ ልጆች የአደጋ/ የጉዳት መከላከያዎች መጠቀም አለመጠቀማቸውን በተመለከተ ሲሆን ፣ በጥያቄው መሠረት ልጆቹ በሥራ ላይ የአደጋ መከላከያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ተጠይቆ ከተጠቀሙ ኮድ 1 ያልተጠቀሙ ከሆነ ግን ኮድ 2 መመዝገቡን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ዓምድ 608:- ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ውጭ በምሽት ትሠራለህ/ትሠሪያለሽ?

በዚህ ጥያቄ ልጆቹ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ በማታ ወይም በምሽት መሥራት አለመስራታቸውን ለማወቅ ሲሆን፣ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ በምሽት ለማይሠሩ ኮድ 1 ሲሞላላቸው በተደጋጋሚ ለሚሠሩት ኮድ 2 ይሰጣቸዋል:: ነገር ግን አልፎ አልፎ ለሚሠሩት ኮድ 3 ሲሞላላቸው በጣም አልፎ አልፎ፣ ለሚሰሩት ደግሞ ኮድ 4 መመዝገቡን በትክክል ማረጋገጥ ይኖርብናል::

ዓምድ 609:- የምትሠራው/የምትሠሪው ለማን ነው?

በዚህ ዓምድ የተፈለገው ልጆች ስራን ለመሥራት የሚያስገድዳቸውን ምክንያት በተወሰነ መልኩ ለማወቅ ሲሆን የሚሰጡትንም ምክንያት ሊለያይ ይችላል:: በግል ወይም ለራሴ ነው የምሰራው

ለሚሉት ሳይቀጠሩ የራሳቸውን ስራ ለሚሠሩ ልጆች ኮድ 1 የሚመዘገብላቸው ሲሆን ለቤተሰቤ ብዬ ነው የምሰራው ለሚሉት በወላጅ/አሳዳጊ/ወይም ለቤተሰባቸው ለሚሠሩ ኮድ 2 ሲሞላላቸው ነገር ግን ከቤተሰብ ውጪ ለሌላ ግለሰብ /ድርጅት/የምሰራው ለሚሉት ኮድ 3 ይሞላላቸዋል። ነገር ግን ከዚህ የተለየ መልስ ለሚሰጡት ደግሞ ምክንያቱ ተገልጾ ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

*ዓምድ 610:- ሥራ ሠርተህ/ሽ ያገኘኸውን/ሺውን ክፍያ ለማን ትሰጣለህ/ትሰጪያለሽ?*

በዚህ ዓምድ ልጆች በሰሯቸው ስራዎች ምክንያት የሚከፈላቸውን ክፍያዎች ማን እንደሚገለገልበት ለማወቅ ሲሆን፣ ክፍያው በገንዘብ፣ በዓይነት ወይም በሁለቱም ሊሆን ስለሚችል እንዲሁም በወላጅ/አሳዳጊ/በቤተሰባቸው ድርጅት ውስጥ ሳይከፈላቸው የሚሰሩ ሊኖሩ ስለሚችሉ ልጆቹ የሚያገኙትን ክፍያ ለማን እንደሚሰጡ ተጠይቀው በሚሰጡት መልስ መሠረት ክፍያውን ለግላቸው የሚያውሉት ከሆነ ኮድ 1 ለሚኖሩበት ቤተሰብ/ወላጅ/ ወይም አሳዳጊ ከሆነ ኮድ 2 ከሚኖሩበት ከቤተሰባቸው/ከወላጅ /ወይም አሳዳጊ ውጭ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጡ ከሆነ ኮድ 3 ከተዘረዘሩት አማራጮች ውጭ ከሆነ ደግሞ ኮድ 4 ይሞላና ምክንያቱ ይገለፃል። እንዲሁም በቤተሰባቸው ድርጅት ወይም /ከቤተሰባቸው ውጭ ለሌላ ግለሰብ/ ድርጅት ውስጥ ሳይከፈላቸው ለሚሠሩ ኮድ 5 መሞላቱን ማረጋገጥ ይኖርብናል። እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን አንዳንድ መረጃ ሰብሳቢዎች አዲስ የተጨመረውን ኮድ ባለማስታወስ ሳይከፈላቸው የሚሰሩ በኮድ 4 «ሌላ» የሚለውን ኮድ ሊሰጡ ስለሚችሉ በዚህን ጊዜ በዓምዱ መመዝገቢያ ላይ የተመዘገበው ያለክፍያ/ሳይከፈላቸው የሚል ከሆነ በኮድ መፃፊያ ቦታ ኮድ 5 በመፃፍ ማስተካከል ያስፈልጋል።

*ዓምድ 611:-* ባፉት 6 ወራት ውስጥ በሥራ ቦታ በስራው ምክንያት ህመም/የአካል ጉዳት/ደርሶብህ/ደርሶብሽ ያውቃል?

በዚህ ጥያቄ ልጆች 2 ዓይነት የተለያዩ መልሶች እንዲመልሱ ይጠበቃል። ይኸውም ባለፉት 6 ወራት በሥራ ላይ ህመም/ጉዳት/ደርሶብናል ብለው ለመለሱ አዎን ኮድ 1 ሲሞላላቸው ምንም አይነት ህመም/የአካል ጉዳት/ ላልደረሰባቸው ደግሞ የለም ተብሎ ኮድ 2 የሚመዘገብላቸው ሲሆን በዚህ ጥያቄ ኮድ 1 ለመለሱ ሁሉ የሚቀጥለው ጥያቄ 612 ይጠየቅላቸዋል። በአንፃሩ ደግሞ ኮድ 2 ለመለሱ ጥያቄው የሚያበቃ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

*ዓምድ 612:-* ይህ የደረሰው የጉዳቱ ወይም ህመሙ ዓይነት ምን ነበር ? የደረሰው ጉዳት/ ህመም አይነት ይግለፁ።

ይህ ጥያቄ የሚጠየቁት ልጆች 611 ላይ ባለፉት 6 ወራት በሥራ ላይ ህመም/የአካል ጉዳት ደርሶብናል ብለው ኮድ 1 ለመለሱ ሁሉ ነው በስራ ምክንያት ህመም/የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ልጆች ሁሉ የህመሙ/የአካል ጉዳቱ ዓይነት መፃፉንና ትክክለኛ ኮድ መሞላቱን ማረጋገጥ ይገባናል።

**ማሳሰቢያ:- አማራጭ መልሶችም ለጥያቄ 606 ከተሰጠው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።**

## ዕዝል 1 የዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምህረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1998 ዓ.ም ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተወለድበት | 1884 | 114 |
| 2 | ዝዋይ የተወረረበት/ከጅቡቲ እስከ አዲስ አባ ያለው የባቡር መስመር የተዘረጋበት | 1886 | 112 |
| 3 | የወላሞ ዘመቻ የተደረገበት | 1887 | 111 |
| 4 | ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከኢጣሊያ ወታደር ጋር በኩዓቲት ላይ ጦርነት የገጠሙበት | 1887 | 111 |
| 5 | ራስ መንገሻ በኩዓቲትና በሰንዓፌ ላይ በኢጣሊያ ድል የሆኑበት | 1887 | 111 |
| 6 | የዓድዋ ድል የተገኘበት | 1888 | 110 |
| 7 | ንጉስ ተክለሃይማኖት ያረፉበት | 1893 | 105 |
| 8 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ምጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት | 1897 | 101 |
| 9 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 100 |
| 10 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 98 |
| 11 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 96 |
| 12 | አፄ ምኒልኪ ያረፉበት /ልጅ እያሱ የነገሱበት | 1906 | 92 |
| 13 | ራስ ሚካኤል በወሎ በትግራይና በጎጃም የነገሱበት | 1907 | 91 |
| 14 | ንግስት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 89 |
| 15 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 89 |
| 16 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 88 |
| 17 | የኀዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 87 |
| 18 | ልጅ እያሱ የተያዙበት | 1913 | 85 |
| 19 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኀበር አባል የሆነችበት | 1916 | 82 |
| 20 | የባሪያ ነፃነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 82 |
| 21 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 81 |
| 22 | ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1918 | 80 |
| 23 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 79 |
| 24 | ንግስት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 76 |
| 25 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር | 1922 | 76 |
| 26 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የነገሱበት | 1923 | 75 |
| 27 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 71 |
| 28 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 70 |
| 29 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 69 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 30 | በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 68 |
| 31 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | 65 |
| 32 | ኢጣልያን ድል የተመታችበት | 1933 | 65 |
| 33 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | 61 |
| 34 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 55 |
| 35 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 55 |
| 36 | የሸንቁጤ ረሃብ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 48 |
| 37 | ዘመነ አንበጣ | 1951 | 47 |
| 38 | እነጄኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን መንግሥት ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 45 |
| 39 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሃደችበት | 1955 | 43 |
| 40 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 43 |
| 41 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 35 |
| 42 | የወሎ ድርቅ | 1965 | 33 |
| 43 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 32 |
| 44 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 31 |
| 45 | የዕድገት በኅብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የተከበረበት | 1967 | 31 |
| 46 | የገጠር መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 31 |
| 47 | የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 31 |
| 48 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 31 |
| 49 | የራዛ ዘመቻ የታወጀበት | 1969 | 29 |
| 50 | የሱማሌ ዘመቻ | 1969 | 29 |
| 51 | የእናት አገር ጥሪ የተደረገበት | 1969 | 29 |
| 52 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሠረተበት | 1972 | 26 |
| 53 | የቀይ ኮከብ ዘመቻ | 1974 | 24 |
| 54 | ብሄራዊ ውትድርና የታወጀበት | 1975 | 23 |
| 55 | የመጀመያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሔደበት | 1976 | 22 |
| 56 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው የአብዮት በዓል የተከበረበት | 1977 | 21 |
| 57 | በትግራይና ወሎ ከፍተኛ ረሃብ የገባበት | 1977 | 21 |
| 58 | የሰፈራ ኘሮግራም የታወጀበት | 1978 | 20 |
| 59 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሽት | 1981 | 20 |
| 60 | ኢህአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 15 |
| 61 | ሁለተኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የተንሄደበት | 1987 | 11 |
| 62 | የሽግግር መንግሥት ያከተመበት | 1987 | 11 |
| 63 | ኤርትራ ባደመን የወረረችበት | 1990 | 8 |
| 64 | ባደመ በዘመቻ ፀሐይ ግባት ነፃ የወጣችበት | 1991 | 7 |
| 65 | የኤርትራ ሰራዊት ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ መሬት የወጣበት | 1992 | 6 |